April 30, 2015

ይህ ፅሁፍ ከአራት አመት በፊት አቡጊዳ ድረ-ገጽ ላይ (December 23, 2010) የወጣ ነው። በወቅቱ በአንዳንድ ተቃዋሚ ወገኖች ያየሁት "የአቋም ማስተካከል ወይንም መንሸራተት" ስላሳሰበኝ በጠንካራ ድርጅታዊ መሰረት ላይ የለሉ ድርጅቶች፣ ሻእቢያን አስመልክቶ የሚያሳዩት የዋህነት ለትግሉ ከሚሰጠው ጥቅም ጉዳቱ ያመዝናል ብዬ ስለማምን፣ አንዳንድ እውነታዎችን በመጥቀስ በረጋ መንፈስ እንዲመረምሩት ለማሳሰብ ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የሚሻ ማናቸውም ድርጅት፤ የትግሉ እንብርት ኢትዮጵያ ውስጥ እንጂ የኤርትራ በረሃ እንዳልሆነ ተረድቶ፤ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን ተደራጅቶ ማደራጀቱን መሃል አገር ማድረጉ አማራጭ የለለው መሆኑን መገንዘብ ያሻል። በዚህ መንገድ ድርጅትንና ህዝብን ካደራጁ በኋላ ትግሉን ወደፊት ለማራመድ ለራስ ጥቅም ከማንም ጋር የሚደረግ ትብብር ደልዳላ መሰረት ስለሚኖረው የስኬት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል።

ጠንካራ መዋቅራዊ መሰረት የለለውና የህዝብ ድጋፍ ከጎኑ ያልያዘ ድርጅት ግን፣ ከኢሳያስ በሚገኝ ትብብርና ድጋፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ትግል አካሂዳለሁ ብሎ ቢያስብ፣ ብዙ መቶ ወታደሮች ከነሙሉ ትጥቃቸው ይዞ ኤርትራ ገብቶ ለአመታት የውሃ ሽታ የሆነውን የጄነራል ከማል ገልቹን ልምድ ማስታወስ የግድ ይላል።

በቅርቡ ሁለት ወጣት የኢሳት ጋዜጠኞች በኤርትራ ቆይታቸው ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ሳዳምጥ፣ ሺ ቃለ ምልልስ የማድረግ ልምድ ያለው ኢሳያስ አጋጣሚውን በመጠቀም፣ የራሱን ትክክለኛነት፣ቅን የህዝብ አገልጋይነትና፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የነበረውንና ያለውን ቅን አስተሳሰብ፣ እንዲወሸክትልን በር ከመክፈት ሌላ የፈየደው አለመኖሩን ስገነዘብ ይሄ ሻእቢያን አስመልክቶ የሚታየው "የዋህነት" ምን ድረስ ሊሄድ ነው የሚል ጥያቄ አጭሮብኛል። እርግጥ ነው በመላ አሜሪካ እየዞርን ስለ ቃለ ምልልሱ ገለጻ እናደርጋለን ብለው የነበረ ቢሆንም በሰዎች ጫናም ይሁን በሌላ ማቋረጣቸው የኢሳያስን የተበላሸ ተክለ ሰውነት ለማደስ ከሚደረግ ሩጫ ሊገታቸው ችሎ ነበር።

ሆኖም ሰሞኑን ደግሞ ሌላ አቋራጭ ተፈልጎ "ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ" የሚል ጉባዔ ተዘጋጅቶ በፀረ-ኢትዮጵያዊነቷና በኢሳያስ አምላኪነቷ የምትታወቀውንና ሌሎች አፍቃሪ ኢሳያስ ሰዎችን ለኢትዮጵያ በጎ ከሚያስቡ ምሁራንና የመንግስት ተቃዋሚዎች ጋር ሰብስቦ ስለአካባቢው ሰላም ብልፅግናና ዴሞክራሲ እንወያያለን ማለት ከ "የዋህነት" አልፎ ሻዕቢያን አስመልክቶ ወደ ምርኮኝነትና ተንበርካኪነት የተጀመረ ጉዞ ያስመስለዋል።

ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በቋንቋ፣ በባህልና በሀይማኖት ካላቸው መቀራረብ ባሻገር በሚጋሩት ረጅም ወሰን ምክንያት በመሃላቸው መልካም ግንኙነት የመኖሩ አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። እድሜ ለሻዕቢያና ለህወሃት ወንድማማች ህዝቦች ሁለት ሀገር እንዲሆኑ ቢገደዱም በሁለቱም ሀገሮች ለዴሞክራሲና ለብልጽግና የሚደረጉ ትግሎች በመርህ ላይ የተመሰረተ ድግግፎች ካደረጉ በሁለቱም ሀገሮች ያሉትን አምባገነኖች አውርደው በቀጠናው ሰላምን ለማምጣት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ እሙን ነው። ከዚህ ውጭ ኢሳያስን ከመሰለ ፍጹም አምባገነን ጋር አላቻ ጋብቻን መፍጠር ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ትግል አደናቃፊ እንጂ ወደፊት የማያራምድ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

አበጋዝ ወንድሙ

# ሻዕቢያ እንደ አጋር?

የኢትዩጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ተቃዋሚ ድርጅት ከማናቸውም ቡድን ድርጅት ወይም ሀገር ጋር ፣ ለትግሉ ይጠቅማል ትግሉንም ወደፊት ያራምዳል ብሎ እስካሰበና እስካመነ ድረስ ግንኙነት ማድረጉ የሚጠበቅ ነው።

ሆኖም ግን፣ ከማንም ቡድን ጋር የሚመሰረተው ማናቸውም ግንኙነት፤ ትክክለኛነት ወይም ወቅታዊነት የሚመዘነው ከመርሀ አንጻር ብቻ ሳይሆን፣ ታሪካዊ ተመክሮንም ያካተተ መሆኑን በመመርመርም ጭምር መሆን ይኖርበታል።

ይህንን አስተያየት እንድጽፍ ያነሳሳኝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ወገኖች፤ በተለይ ደግሞ ግንቦት ሰባት በመባል የሚታወቀው ድርጅት፤ ሻዕቢያን በሚመለከት እያሳዩ ያሉት ወገንተኝነትና የአቋም ማስተካከል ወይንም መንሸራተት እያሳሰበኝ ስለመጣ ነው።
ለዚህም፤ ለአብነት ያህል፣ በቅርቡ *የግንቦት 7 ድምፅ* በሚለው መጽሄት ላይ የወጡ፤ ይህንን አስተሳሰብም የሚያንጸባርቁ ጽሁፎችን እጠቅሳለሁ፦

"...በቂ ምክንያት ሳይኖር ወደ ጦርነት (የባደመን) ገብቶ ከዚያም የተስማማበትን የአልጀርስ ስምምነት በመጣስ..." (የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 55 ግንቦት 27 ዓ.ም.ገጽ 3)

"ክፍለ አህጉሩን እያመሰ ያለውን ወያኔ" (*የግንቦት ድምፅ* ቁጥር 91 የካቲት 4 2002 ዓ.ም. ገጽ 2)
ምእራባውያን አርቀው ለማየት ባለመፈለጋቸውና በአጭር ግዜ መፍትሄ ፍለጋ ላይ በመጠመዳቸው ወያኔ አካባቢውን በማመስ እሱ ብቻ የመረጋጋት ሀይል መስሎ እንዲታይ...." "በኤርትራ ላይ የተጣለው ፈሩን የሳተ ማእቀብ ነው" "ለአካባቢው ሰላም መደፍረስ መሰረታዊ ምክንያት የሆነው ወያኔ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች የጋራ ትግል መወገድ ይኖርበታል" (*የግንቦት ድምፅ* ቁጥር 87 ጥር 6 2002 ዓ.ም. ገጽ 2)

ሻዕቢያ ከተመሰረተ ከዛሬ 38 አመት ጀምሮ፣ ኢትዮጵያን፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካና ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ድርጅቶችን በሚመለከት፣ እንደ ድርጅት የተጫወታቸውን ሚናዎች ስንገመግም በመሰረቱ አሉታዊ እንደሆኑ መገንዘብ ለማንም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ይሆናል።
*<u>ይሄም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ሻዕቢያ በተፈጥሮው ሸረኛ ወይንም ክፉ ስለሆነ ሳይሆን፣ ሻዕቢያ ይዞት የተነሳው፣ ያራመደውና የተገበረው አላማ በኪታዊ ሊሆን የሚችለው ይህንን ኢትዮጵያን አጥፊ ጎዳና የተከተለ እስከሆነ ድረስ ብቻ ስለነበር ነው።</u>*
ሻእቢያ ከመቋቋሙ ቀደም ብሎ የጀብሀ አባላት የነበሩ የኤርትራ ብሄርተኞች በሃገር ቤት የተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የነበራቸውን ኤርትራውያን ተማሪዎች ከአጠቃላይ የተማሪው እንቅስቃሴ ራሳቸውን እንዲያገሉ ያደረጉትን ጥረት፣ ተደራጅቶ በገሀድ ከወጣ በኋላ በሰፊው የቀሰቀሰና ያሳካ ድርጅት ነው። ይሄ እንቅስቃሴና የመነጠል ተግባር በውጭ ሀገር ተደራጅተው የሚታገሉ የተማሪው እንቅስቃሴ አባላትንም የጨመረ ነበር።

ከዚህ አልፎ እኒህ በታላቅ ግፊት የተነጠሉ ግለሰቦች ስለህብረ ብሄር ትግል ያላቸው ጠንካራ እምነት ወደፊት ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ዴሞክራቲክ ሀይሎች ጋር አጋርነት ሊፈጥሩ ይችላሉ በሚል ፍርሀት ጭምር አጉያው ካስገባ በኋላ "መንከአ" በሚል የጨፈጨፈ ድርጅት ነው።

ሻዕቢያ የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለየ መልኩ ተጨቁኗል በሚል የተሳሳተ ቀመር የተነሳሉ ወጣት ብሄርተኞችን ለሱ በሚጠቅመው አቅጣጫ መክሮና ረድቶ ለአላማውም ስኬት ከአሥር ሺህ የሚበልጡ የትግራይ ወጣቶችን አስገብሮ፣ ለእኛ ደግሞ ላለፉት አስራ ስምንት አመታት ይህንን ወያኔ የተባለ እኩይ ቡድን እንድንሸከም ትልቅ አስተዋጾ ያደረገ ድርጅት ነው።
ኢህአፓ ከተቋቋመ ጀምሮ፣ ለረጅም ጊዜ ፣ ምንና ምን አይነት አሉታዊ ድርጊቶችን ይፈጽምበት እንደነበር ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ በተባለው መጽሀፍ ውስጥ በሰፊው ያብራራው ጉዳይ ስለሆነ እንደገና ማየት መልካም ነው።

ወያኔ አዲስ አበባን ለመያዝ ባደረገው እንቅስቃሴ ታንከኛ ብርጌዱን ይዞ የመጣው ሻዕቢያ፣ የኦነግ አመራር አባላት ላይ ያለውን ተደማጭነት በመጠቀም የኢሃአዴግ ጦርን የኢትዮጵያ ጦር ተብሎ እንዲሰየም ያግባባ፣ በዚህም ሳቢያ ነባሩ ጦር እንዲበተንና፣ የኢትዮጵያ የመከለከያ ሀይል ተቋማት እንዲፈራርሱ ትልቅ ሚና የተጫወተ፤ በዚህም መዘዝ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ጦር ባንድ ብሄርና ባንድ ድርጅት ስር እንዲወድቅ ታላቅ አስተዋጾ ያደረገ ድርጅት ነው።

ሻዕቢያ በ1998 ባድመን አስመልክቶ በጫረው ጦርነት ሳቢያ እስከ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ሕይወት መቀጥፍና ለሌላ ብዙ ሺህዎች መሰደድ እንዲሁም ንብረት መውደም ዋና ተጠያቂ የሆነ ድርጅት ነው።

ይሄ ኢትዮጵያን በሚመለከት ካካሄዳቸው አስከፊ ተግባራት በተጨማሪ ላለፉት አስራ ስምንት አመታት ነፃ አወጣኋችሁ ያላቸውን ኤርትራውያንን፤ ባንዳንዶች ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች እምነት፤ ከባርነት ባልተናነሰ መልኩ ቁም ስቃይ የሚያበላ መንግስት በምን ተአምር ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄደው የህግ የበላይነትና ዴሞክራሲን ለማስፈን ለሚደረገው ትግል አጋር ሊሆን ይችላል ብሎ ሊታሰብ እንደሚችል በጣም ግራ የሚያጋባ ሆኖ ነው የሚታየኝ።

እርግጥ ነው፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች መሀል ባለው ባህላዊ፤ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ ትስስር አንጻር ሲታይ ምንም እንኳን በቅርብ በመጣ ታሪካዊ ሂደት የሁለት ሀገር ህዝቦች እንድንሆን ብንገደድም ባለን የጂኦግራፊ ቅርበት የተነሳ ከሌላ ሀገር ወይንም ህዝብ የተለየ ተቀራራቢ ግንኙነት እንዲኖረን የግድ ነው። እንደመንግስትም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም አይነት መንግስት ኤርትራ ውስጥ ከሚኖር ማናቸውም መንግስት ጋር ግንኙነት ማድረግ (የግንኙነቱ ጥንካሬና ጥልቀት ሁኔታው የሚወስነው ቢሆንም) መኖሩ ግን የግድ ነው።
ይሄ ግን በመንግስታት ደረጃ የግድ የሚሆነው ግንኙነት እንጂ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ግዴታ ውስጥ የሚይስገባ እንዳልሆነ በግልጽ ሊታወቅ የሚገባ መሆን ይኖርበታል።
"የሻዕቢያን ምንነት አውቀን ለኛ በሚጠቅመን መልኩ ብቻ ልንጠቀምበት በማሰብ ነው ግንኙነታችንን የምናካሂደው" የሚል መከራከሪያ ድርጅቶቹ እንደሚያቀርቡ ከወዲሁ

ብገምትም ይሄንን ተአማኒ ሊይደርግ የሚችል አንጽራዊ ጥንካሬ ግን አላቸው ብዬ ስለማላምን ለመቀበል አስቸጋሪ ይሆንብኛል።
አንጻራዊ ጥንካሬ ሳይኖረው የዚህ አይነት አስተሳሰብ አሚያራምደው አነግ ከራሱ ድርጅታዊ ድክመት ባሻገር የሻዕቢያ ተንኮልና ደባ ተጨምሮበት ለመሰነጣጠቅ ከመዳረጉም በላይ ኤርትራ የሚገኙ አንዳንድ የአመራር አባላቱ እንቅስቃሴ ታግዶ የሚገኝበት ሁኔታን ስመለከት ከሻዕቢያ ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት አግባብነት ትልቅ ጥያቄ ይጋረድብኛል።

ስለዚህ እንደ አንድ ዜጋ ግንቦት ሰባትንና ሌሎች ድርጅቶችን አምማጸነው ቢኖር በኢትዮጵያችን የህግ የበላይነትና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ከበቂ በላይ ጋሬጣዎች ስላሉበት አላስፈላጊና ተጨማሪ ' ሻዕቢያ የተባለ ጋሬጣ እንዳይጨምሩበት ነው።

አበጋዝ ወንድሙ